# ጋሻ ለኢትዮጵያውያን

## Gasha for Ethiopians

## መግለጫ

በረጅም ታሪኳና በልጆቿ ጅግንነት በከበረ ነፃነቷ የሚትታወቅ ኢትዮጵያ አገራችን ባሁኑ ገዜ ኢሃገራዊና ከሐዲ በሆነ አምባገነናዊ ቡድን እየተገዛች ነው። ሕ.ወ.ሓ.ትና እሱ የፈጠረው ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ከተመሠረቱበት ግዜ አንስቶ አያሌ የክህደትና አገር የማፍረስ ክንዋኔዎችን ፈጽሟል። እነዚህ ሓይሎች የመሠረቱት መንገሥት ይህንን እኩይ ዓላማ ለማሳካት በተለያዩ ጊዜያት መልኩን እየለዋወጠ የኢትዮጵያ ህዝብን በማታለል ሥልጣን ላይ ከመቆየት ሌላ፣ ለሃገራዊ ሉዓላውነትም ሆነ ለህዝብ ዳንታ የለውም።

ይህ ኃይል ቀደም ብሎ የጀመረውና እኔ ስልጣን ከለቀቅኩኝ ኢትዮጵያ ትበታተናለች የሚለው የማጭበርበር ተግባሩ እነዳይበቃ፡ ግንቦት 1997 በተካሄደው ምርጫ ህዝብ አልፈልግህም ካለው ወዲህ እኔን ከነካችሁ ኢትዮጵያ የሩዋንዳ ዕጣ ይገጥማታል በማለት የማስፈራራት ዛቻውን በሰፊው የተያያዘው ከመሆኑም በላይ በገጠመው ሽንፈት ምክንያት በብዙ ወገኖቻችን ላይ ይህ ቀረሽ የማይባል ግፍ በመፈጸም ላይ ይገኛል። ይህ አባባል የኢህአደግን ተንኮልና ሴራ በቅርብ ለማያውቁትና ለማይከታተሉት አንዳንድ የዋህ ወገኖች እውነት መስሎ ሊታይ የሚችል ቢሆንም ሃቁና ዋናው ቁምነገሩ ግን ኢህአደግ የተነሳበት ዓላማ የኢትዮጵያውያንን ሰብዓዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ማህበራዊ መብቶች ረግጦ፣ የሃገሪቱን ክብር፣ ነፃነትና ብሄራዊ ጥቅም ለሻዕብያና ለኃያላን የእጅ_አዙር ቅኝ ገዥዎች አሳልፎ በመስጠት በስልጣን ላይ ለመቆየት የሚከተለው ሸር የሞላበትና በጥንቃቄ የተቀመረ ስልት መሆኑን ኢትዮጵያውያን ያውቁታል::

የአንድ አገር የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ችግር በቀጥታ የሚያያዘው ባገሩ ውስጥ ከሚታየው ፖለቲካዊ ሂደት ጋር እንደሆነ የሚያጠራጥር አይደለም። በመሆኑም ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው የፖለቲካ ቀውስና አጠቃላይ ችግር ምንጩ አሁን በስልጣን ላይ ያለው የኢህአድግ መንግሥት የተከተለውና እየተከተለው የሚገኝ ፖለቲካዊ ጉዞ እንደሆነ፣ የኢሕአደግ ተፈጥሮአዊ ባሕሪና መሠሪ ጠባይ ለሚያውቅና ውስብስ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ በቅርብ ለተከታተለ ሁሉ ግልፅ ነው።

በመሆኑም ዛሬ ኢትዮጵያ በከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድቀት ውስጥ ተዘፍቃ ሕዝብ ድህነትና በሽታ እየተፈራረቁበት በችግር አጣቢቂኝ ውስጥ ገብቶ የሚሰቃይባት የጣእረሞት አገር ሆና ትገኛለች። አገራችንን ከእንደዚህ ዓይነት የችግርና የመከራ ዓዘቅት ለማውጣት የሚቻለው ደግሞ ሁሉም ዜጋ ተባብሮ የዓቅሙን ያህል አስተዋፅኦ ሲያደርግና ይህንን ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባብሮ ትርጉም ያለው የልማት ዕቅድ ነድፎ መመሪያ መስጠት የሚችል በሕዝብ የተመረጠና የሕዝብ ይሁንታ ያገኘ መንግሥት ሲኖር ብቻ ነው። በማጭበርበር ሥልጣን ላይ ለመሰንበት የቆረጠው ኢህአዴግ በአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ለማምጣት አልቻለም ብቻ ሳይሆን

- ሥልጣን ላይ የመቆየት ዓላማው ስለሚቃረን - ሰላምና መረጋጋት እንዲኖርም አይፈልግም። በመሆኑም ህዝባዊ አመኔታን ፈጽሞ ማግኘት አልቻለም።

ሰላምና መረጋጋት በሌለበትና የሕዝብ አመኔታ ያልተቸረው ፀረ ህዝብና ፀረ ኣገራዊ ሉዓላውነት የሆነ መንግሥት በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ፣ ባጠቃላይ መላው ሕዝብ ፣ በተለይ ደግሞ ባለንብረቶችና ሙያተኞች፣ - ከረጂም ጊዜ አንጻር ሲታይ - በኢኮኖሚው እድገት ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ እሚንት ነው።
ላገሪቱ እድገትና ግንባታ ሊጠቅሙ የሚችሉ የኢኮኖሚ ኣውታሮች የፖለቲካ ታማኝነታቸውን ባረጋገጡ ካድሬዎችና ሌሎች አድርባይ ግለሰቦች ቁጥጥር ሥር በገባበት፣ የውጭ ባለሃብቶች 'ኢንቨስት' እንዳያደርጉ ደግሞ አለመረጋጋትና ሕግ-አልባነት እንቅፋት በሆኑበት ሁኔታ የኢኮኖሚ እድገት ከቶም ሊመጣ አይችልም።

አንድ አገርንና ሕዝብን አስተዳድራለሁ የሚል መንግስት ቢያንስ አገራዊ ስሜት ይኖረዋል ተብሎ የሚጠበቅ ቢሆንም አሁን ስልጣን ላይ ያለው መንግስት አገራዊ ስሜት የሌለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሆን ብሎ በፀረ ሉዓላውነት አቋሙ የሚታወቅ ሃይል መሆኑ በግልፅና በተግባር ያስመሰከረም ነው።

በደርግ ዘመን የፈሰሰ ደም ሳይደርቅ በግርግር በሻዕቢያ ቁጥጥር ሥር በተካሄደው የማስመሰያ 'ሪፈረንደም' መገንጠልን መርጧል የተባለው የኤርትራ ህዝብ ጉዳይ ሰላምና መረጋጋት ያመጣል እየተባልን የተሰበክን ቢሆንም የተነገረን ሁሉ ህልም ሆኖ መቅረቱንና በተቃራኒው የከፋ ጦርነት ማስከተሉን አይተናል። ተረጋግተውና ስለሩቁም አስበው በሓላፊነት ስሜት የሚወስኑ መሪዎች ያጣው ያልታደለው የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ በጽሞና ሊመክርበት ችሎ ቢሆን ኖሮ የተከሰተው ዓይነት ሓላፊነት የጎደለው ጥፋት ሊደርስ ፈጽሞ ባልቻለ ነበር። ይህ የሁለቱ አምባገነኖች የክህደት ተግባር ዛሬ በሪፈረንደሙ ያልተሳተፈውና ኢትዮጵያውነቱን ለማስከበር በግልፅ ከ'ወያኔ'ና ከሻዕቢያ ጋር ትጥቅ አንስቶ በመፋለም ላይ ያለው ጀግናው የዓፋር ህዝብና በሁለቱም ድርጅቶች የአልጀርስ የተንኮል ስምምነትና ፀረ-አገር ውዲት ወደ ኤርትራ ግዛት እንዲከለሉ በሁለቱ አምባገነን መሪዎች እየተሴረባቸው የሚገኙት የኢሮብ፣ የዛላንበሳ አከባቢ፣ የባዲመና በሌሎችም የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶች ነዋሪ ሕዝብ የሚገኝበት ሰቆቃ የሚያረጋግጡት ይህንን ግልጽ የሆነ የከሓዲነት ተግባር ነው።

## <u>የጥፋት ዘመንን ለማራዘም ጥፋት!</u>

የኢትዮጵያን ህዝብ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ ወዘተ. ከፋፍሎ አንዱን ከሌላው ጋር በማናቆርና ደም በማቃባት በጠላትነትና በዓይነ ቁራኛ እንዲተያይ በማድረግ ሃገሪቱን አዳክሞ ተመቻችቶ የነበረው ኢህአደግ፣ ዛሬ ሕዝባዊ ማዕበል እያዋከበው ከጥፋት ወደ ጥፋት መሸጋገሩን በይፋ እያየን ነው።

ነፃ ምርጫ ሲባል አሸናፊና ተሸናፊ በህዝብ ድምፅ የሚለዩበት ፣ የብዙሃኑን ድምፅ ያገኘ አሸናፊ፣ አነስተኛ ድምፅ ያገኘ ደግሞ ተሸናፊ የሚሆንበት ሂደት መሆኑ ቢታወቅም ፣ ይህ አገዛዝ የተጠቀሰውን ዓለም-አቀፋዊ መስፈርት ተቀብሎ

የሚመጣውን ህዝባዊ ውሳኔ ለመቀበል የሞራል ዝግጁነትም ሆነ ህልም እንዳልነበረው ለብዙ ኢትዮጵያዊያን ከመጀመሪያውም ግልጽ እንደነበረ የሚታወቅ ነው። በግንቦት ወር የተካሔደው ምርጫም ሆነ በድህረ ምርጫ እየታየ ያለው ጭካኔ የተሞላበት ‘ድራማ’ የሚያረጋግጠውም ይህንን ሀቅ ነው። እዚህ ላይ ተገቢ ግንዛቤ ማግኘት የሚኖርበት ጉዳይ ቢኖር፣ ኢህአዴግ የፖለቲካ ፓርቲ ብቻ አለመሆኑን ነው። የአገሪቱ መንግስታዊ የፖለቲካ ስልጣን፣ የመከላከያ ሰራዊት፣ የአገሪቱ አጠቃላይ የፀጥታና የስለላ ሀይል፣ የህግ አውጪ ፤ አስፈፃሚና ተርጓሚ አካልን ጠቅሎ ባንድ ሰው ቢበዛ ደግሞ ቡድን ቊጥጥር ሥር ያስገባ ፣ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን መንግስት በመሆኑ በምንም ዓይነት ተአምር ስልጣን በሰላማዊ ህዝባዊ ምርጫ የማሰረከብ ፍላጎትም ህልምም ሊኖረው እንደማይችል በግልጽ መታወቅ አለበት።

እስካሁን በዓለም ታሪክ የታዩት ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን መንግስታት የሥልጣን ዕድሜቸውን ለማራዘም የማይሉትና የማያደርጉት ነገር እንዳልነበርና እንደሌለ ፤ ያለፈው ልምድ ብዙ አስተምሮናል። ***“እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል”*** ተብሎ በአበው የተተረተውን የእንስሳዋን ተረት የመተርጐም ግዴታ የተጣለባቸው ይመስል የነሱ የግል ጥቅም ከሚነካ ሕዝብንና አገርንም ቢሆን ይዘው ከመጥፋት ወደኋላ እንደማይሉ በታሪክ በተደጋጋሚ ታይቷል። ይህ ክስተት ዴሞክራሲያዊ አሠራርን በሚከተሉና በሚያከብሩ በሕገ-መንግሥታዊ አሠራር በሚያምኑና በሚመሩ አገሮች ውስጥ አይከሰትም። እንደ ኢህአዴግ መሪዎች በሕገ-መንግሥታዊነት የማይመሩ አምባገነኖች በሚገዙት አገር መከሰቱ ግን ፈጽሞ የማይቀር ነው። ኢህአደግ እነዚህን የአምባገነኖች ባህሪያት በሚገባ ስለሚጋራ እየተከተለው የምናየውም ከላይ የጠቀስነው ይህንኑ የጥፋት ጎደና ነው።

በዴሞክራሲያዊ አሠራርና፣ ሥርዓተ-መንግስት የሚተዳደሩ ሕዝቦች እንደ አንድ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ገፀ-ባህሪ የሚያዩትና የሚቆጥሩት መሪዎቻቸውን በነፃ የመምረጥ የተለመደ አሰራር፣ በአምባገነኖች አገዛዝ ሥር የሚማቅቁ ሕዝቦች ያለ ትግልና ህዝባዊ ዓመፅ ሊጎናፀፉት ይችላሉ ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም። የነዚህን ከላይ በመጠኑ የገለፅናቸውን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገፀ-ባህሪያትን ከአምባገነንነት ባህሪ ጋር ለማነፃፀር ይረዳ ዘንድ ፤ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ቀጥለን እንጠቅሳለን።

1. በአንድ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሚተዳደር አገር ውስጥ ፣ በህዝብ የተመረጠ መንግሥት ሥልጣን ሲጨብጥ በተወዳደረበትና አስቀድሞ ለህዝብ ባደረገው የተመረጠበት ‘ፕላት ፎርም’ መሠረት ቃሉን ማክበርና መፈጸም ካቃተውና ለህዝብ የገባውን ቃል እውን ማድረግ ባይችል በገዛ ፈቃዱ ሥልጣኑን በመልቀቅ አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ማድረግ የተለመደ ተግባር ነው። ይህንን አሠራር አምባገነኖች እንደውርደት ይቆጥሩታል።

2. በህዝብ የሚመረጥ መንግስት፣ የአገሪቱን ሰላምና ፀጥታ ማስከበር ካልቻለ፣ የህግ የበላይነትን ማክበርና ማስከበር ካቃተው፣ የአሠራርና የአሰተዳደር ግልፅነትን ቢጎድለውና አገርና ህዝብን በሚጠበቅበት መንገድ ማስተዳደር ካልቻለ ድክመቱን ተቀብሎ ፣ ህዝቡ የጣለበትን ሓላፊነት ለመወጣት ብቃቱ

የለኝም ብሎ በራሱ ፈቃድ ወይም ደግሞ በህዝብ ግፊት ስልጣኑን ለባለቤቱ ለመረጠው ህዝብ ያስረክባል። አምባገነኖች ህዝብ የሰጣቸው ሥልጣን የላቸውምና ይህንን ዓይነት ነገር እንኳን ሊያደርጉት ለማለምም ይከብዳቸዋል።

3. በህዝብ የሚመረጥ መንግስት የተከተለው ፖሊሲም ሆነ ያወጣው መመሪያ በተግባር ሲተረጎም ያልተፈለገ ውጤት ቢያስከትል ለደረሰው ጥፋት ሓላፊነቱን ሙሉ በሙሉ በመሸከም ሥልጣኑን ለመረጠው ህዝብ እንዲያስረክብ በሕግ ይገደዳል። አምባገነኖች ግን ሕግ አያውቁምና ስለ ሕግና ሕጋዊነት ሊጨነቁ አይችሉም።

4. መንግስት፣ የተሰጠውን ኃላፊነት ከዘነጋ ወይም ስልጣኑን ያላግባብ ከተጠቀመ የአገሪቱ ብሄራዊ ፀጥታ፣ ብሔራዊ የስነ ምግባር ቁጥጥር ባለስልጣንና ሌሎች አገራዊ ተቋሞች በሥልጣን የሚባልገውን በህግ ፊት ቀርቦ እንዲቀጣ ያደርጋሉ። አምባገነኖች በሚገዙት አገር ውስጥ ግን ገገርዎች ራሳቸውን ከሕግ በላይ ስለሚያስቀምጡ የሚጠይቁበት እንጂ የሚጠየቁበት ሕግ አይደነግጉም ፤ ቢደነግጉም አይገዙበትም። ሰለዚህ ባለሥለጣኖችን መክሰስ የማይተለም ይሆናል።

ከዚህ አንፃር ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የምናየው እንኳን ለእኛ - ለኢትዮጵያውያን - ለዓለም ሁሉ ግልፅ ከሆነ ቆይቷል። የጦር ሃይል በማዘዝ እናቶች፣ ህፃናት ወዘተ. ሳይለይ ህዝብን በጠራራ ፀሃይ የሚያስረሽን፣ የህዝብን ድምፅ ያለምንም ሃፍረት በጉልበት ቀምቶ አችናፊው እኔው ነኝ ብሎ የሚያውጅ፣ በዓለም ፍ/ቤት ሆን ብሎ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ መሬት/ግዛት ለጠላት ካስረከበ በሁዋላ አቸንፈናል ብሎ ዳንኬራ የሚያስመታ... 'መንግስት' ነው ተሸክመን የምንገኘው።

ሰለዚህ አገራችን በማን አህሎኝነት ስሜት በተወጠረ፣ የሕዝቡን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ረግጦ፣ የህግ ተገዢ አልሆንም በሚል እብሪተኛና ኣምባገነን ቡድን መዳፍ ስር በመማቀቅ ትገኛለች። የህዝብ ብሶት እየገፋ በመምጣቱና ገዥው ክፍል በስጋት በመወጠሩ ሰላማዊውን ተቃውሞ በጭፍጨፋና በግድያ ለማስቆም ቆርጦ ተነስቷል። ስለዚህም በሕዝብ ላይ ጭፍን የሆነ ግድያና፣ አፈና ያለማቋረጥ በማካሄድ ላይ ነው። **አንድ መንግስት እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ "የጥፋት ዘመን ለማራዘም ጥፋት" ይጨምራል። የአቶ መለሰ ዜናዊ አስተዳደር የሚከተለው ያለው ይህንኑ የጥፋት ጎደና እንደሆነ ገልፅ ይመስለናል።**

ህዝብም የሚደርስበት ወከባ፣ እስራትና ግድያ ያንገፈግፈውና መንግሥትን በኃይል ለመገርሰስ ይነሳል። ይህንን ለማድረግ ለጊዜው ዓቅም ቢያንሰው በትእግሥት ኣመቺ ጊዜን ይጠብቃል እንጂ አምባገነኖችን ለዘላቂ ሽርሩ የሚልበት አንጀት ሊኖረው አይችልም። ዛሬ እየታዘብነው እንዳለው ያገዛዙ ታማኞች በየሄዱበት ጥገኝነት መጠየቅ ማለት የአምባገነን አገዛዙ ውስጣዊ ድክመቶች ሥር መስደዳቸውና ሊጠገኑ የማይችሉበት ደረጃ ላይ መድረሳቸው ያመላክታሉ። ይህም ህዝባዊ ትግሉ አገዛዙን በማያዳግም ምት እየወቀረው እንዳለ ያሳያል። ያገዛዙ

ዕድሜም ከቀን ወደ ቀን እያጠረ በመሄድ አይቀሬውን የሞት ፅዋ ይጎነጫል። ይህ በኢትዮጵያም አይቀሬ ነው።

ከዚህም ሌላ ዛሬ ህዝባችን በጎረቤት አገሮች በስደት እየተሰቃየና እየሞተ ነው። የኢህአደግ መንግስት ለአገራቸው እንዳይሠሩ እንቅፋት ስለሆነባቸው ሳይወዱ ወደ ውጭ አገሮች የጎረፉት ምሁራንና ሙያተኞች ጉዳይ እንዳይበቃ የተቃዋሚ ድርጅቶች ደጋፊ ስለሆኑ ወይም የኢሕአዴግ ፖሊሲን ባለመደገፋቸው ብቻ የከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች፣ የሕክምና ዶክተሮችና ሌሎች ባለሞያዎች ወዘተ. ከሥራ ተባረዋል ታሥረዋልም። በዚህም አገሪቱ ምሁር አልባ ሆና እየቀረች ነው።

እነዚህ ከላይ ያተትናቸውና ሌሎች ጉዳዮች እጅግ በጣም ስለሚያሳስቡንና ለህዝባችንና ላአገራችን የሞራልና የሕሊና ግዳጅ ስላለብን፣ ተደራጅተን ድርሻችንን ለማበርከት በተለያዩ ክፍለሀገሮች የምንገኝ ኢትዮጵያውያን፣ በርካታ ጊዜ በያለንበት አገር አንዳንዴም ሁሉ የተሳተፈበት ተሌኮንፈረንሶች በማዘጋጀት ሰፊ ውይይት ካደረግን በኋላ መጋቢት 30 1998 ባደረግነው ጠቅላላ ጉባኤ ሲቪክ ማህበር ለማቋቋም ተስማምተናል። ባለፉት ሁለት ወራት አስፈላጊ ዝግጅቶች ካጠናቀቅን በኋላ በሰኔ 10 1998 እንደገና ባደረግነው ጠቅላላ ስብሰባ ማህበራችንን ይፋ ለማድረግ ወስነናል። የማህበራችን ስም *'ጋሻ ለኢትዮጵያውያን'* እንዲሆንም ተስማምተናል። ዓላማችን በሚከተሉት ሁለት አንቀፆች ሊጠቃለሉ ይችላሉ።

ሀ) በኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን፣ ፍትሕና የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ እንዲከበሩ፣ ብሄራዊ ዕርቅና ሃገራዊ አንድነት እንዲዳብርና እንዲጎለብት፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እንዲከበር አቅማችን የሚፈቅደውን አስተዋፅኦ ለማድረግ።

ለ) የኢትዮጵያ ህዝብ ለኢህአዴግ ከፋፋይ ፖሊሲ ሳይበገር በብሔረ-ሰብና ሃይማኖትም ሳይከፋፈል ዛሬም እንደ ጥንቱ ተባብረውና ተከባብረው በወንድማማችነት እጅ ለጅ ተያይዘው በጋራና በፍቅር የሚኖሩባት አገራቸውን የመታደግ ሓላፊነታቸውን በመወጣት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚያደርጉትን ትግል በመደገፍ ድርሻችንን ለመወጣት።

ጋሻ ለኢትዮጵያውያን በመሥራች ጉባኤው አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያለውን ድጋፍ እነደሚከተለው ይገልጻል።

1. በግንቦቱ የምረጫ ወቅትና ከምርጫውም በኋላ ጠቅላይ ሚንስትሩና ተባባሪዎቻቸው እንዲሁም አንዳንድ ሌሎች ፖለቲከኞች በብሔረሰቦች መካከል ጥላቻ እንዲኖር ብሎም ሕዝብ ለሕዝብ እንዲጋጭ ለማድረግ የፈጠሩዋቸውን አሉባልታዎችና እኩይ ተግባሮችን ማህበራችን አጥብቆ ይኮንናል።

2. የኢትዮጵያ ሕዝብና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከየአቅጣጫው የሚናፈሱት አገርና ህዝብን ሊከፋፍሉ የሚችሉ የጥላቻ ቅስቀሳዎችን አምርረው እንዲታገሉትና የአገራችንና የህዝቦቻችንን አንድነት ለማስጠበቅ ድርሻቸውን እንዲወጡ ጥሪውን ያቀርባል። ይህንን አለማድረግ አቶ መለስና ግብረአበሮቻቻው ባመቻቹብን ወጥመድ ውስጥ መግባት መሆኑንም ያስገነዝባል።

3. በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች፣ በነፃ ጋዜጠኞች፣ በሠራተኞችና፣ በመምህራን ማህበራት፣ በጠበቆች፣ ወዘተ. ላይ የተካሄደውና እየተካሄደ ያለውን ዘመቻና እሥራት እንዲቆምና የሙያ ሆኑ ሌሎች ህዝባዊ ማህበራት በነፃ የመደራጀት መብታቸው እንዲከበር አጥብቆ ይጠይቃል።

4. ዲሞክራሲን ለመገንባት እየጣርኩ ዲሞክራሲ እንዲዳብር የሚረዳኝ ተቃዋሚ አጣሁ እያለ ሲባዝን የነበረው የሕ.ወ.ሓ.ት/ኢ.ህአዴግ መንግስት ከግንቦቱ ምርጫ በኋላ እየታየ ያለውን በ'ቅንጅት' አመራሮች ፤ አባሎች ፤ ደጋፊዎችና በሌሎች የፖለቲካ ድርጅት አመራሮች አባሎችና ደጋፊዎች፣ በተማሪዎችና በሌሎች ወጣቶች፣ እንዲሁም ወንድ-ሴት ሳይል በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈፀመውና እየፈጸመ ያለውን ግድያና እሥራትን እያወገዘ፤ በፖለቲካ አቋማቸው ምክንያት በየእስርቤቱ የታጐሩ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላት እንዲሁም ተራ ዜጎች ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ እንዲፈቱና በግድያና በሰብአዊ መብት ረገጣ እጃቸውን ያስገቡትም በሕግ እንዲጠየቁ እንዲደረግ አጥብቆ ይጠይቃል።

ኢትዮጵያ በልጆችዋ የተባበረ
ሃይል ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!

ጋሻ ለኢትዮጵያውያን
ሰኔ 1998